# ምነው በኢሕአፓ ላይ ጩኸት በረከተ?

አስረስ ደመቀ

ይህችን አጭር አስተያየት እንድሞነጫጭር ያነሳሳኝ ሰሞኑን “የ ኢሕአፓ አንድነት ሲምፖዚየም ” በሚል ርዕስ የተሰራጨ በራሪ ወረቀት “ ተመለከትኩና በጥሪው ላይ የጥናት ፅሁፍ አቅራቢ ተብለው ከጋበዙ 7 እንግዶች ውስጥ በተለይ አወዛጋቢ ታሪክ ያላቸውን የሁለት የቀድሞ የኢሕፓ ዓመራር ኮሚቴ ዓባላትን ስም ማየቴና የጥሪው ባለቤት የሆነውን ክፍል የቅርብ ጊዜ ታሪክ እንዳስታውስ ስላደረገኝ፣ እስቲ በመጀመሪያ ስለ አዘጋጁ ክፍል ያስታወስኝን ላካፍል፡

በ1997 ዓ.ም የወያኔው አለቃ የነበረው መለስ ዜናዊ ኢሕአፓ ሁለገብ አቋሙን ስቦ አፊዳቪት /ለወያኔ እታዘዛለሁ ብሎ ከፈረመ አገር ውስጥ በግልፅ የመንቀሳቀስ ህጋዊ መብቱ ይጠበቅለታል በሚል ሆን ብሎ ያሾለከው የሚመስል ዜና፣ በአንድ በጊዜው ቀቢጸ ተስፋ ባጠቃው የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴ ዓባል የነበረ ግለሰብ ጆሮ ያገኘና፣ ይ ኸው ዓመራር ግለሰብ፣ ቅድመ ሁኔታውን ተቀብሎ (የወያኔን አፊዳቪት ፈርሞ) በአቋራጭ ድርጅቱን በራሱ መሪነት ይዞ ገብቶ የወያኔ ተለጣፊ በማድረግና ወንበር ለመያዝ በነበረው ከንቱ ፍላጎት ፣ “አገር ውስጥ ገብተን በህጋዊና በሰላማዊ መንገድ መታገል እንችላለን” በሚል ውስጥ ለውስጥ ድጋፍ በማሰባሰብ በድርጅት ውስጥ ቡድን ፈጥሮ በሚስጥር ሲንቀሳቀስ መቆየቱ ታወቀ። የቡድኑ ውስጥ ለውስጡ እንቅስቃሴ እየሰፋ መጥቶ ግልፅና አደገኛ ሁኔታ መፈጠሩን የድርጅቱ ዓመራር እንደተረዳ፣ የድርጅቱ ህልውና አደጋ ላይ እንደወደቀ በመረዳት ጠቅላላ ዓባላቱ መፍትሄ እንዲፈልጉ (ረዥሙን ሃተታ በአጭሩ ለመጠቀም) በዚሁ ግለሰብ ጠያቂነት ልዩ ጉባኤ ጠራ። በመሆኑም በመስከረም ወር 1999 ዓ.ም ልዩ ጉባኤ ተካሄደ።

ይህ የድርጅቱ ከፍተኛ አካል፣ ችግሮቹን በውይይት በመፍታት አንድነቱን ጠብቆ ይወጣል ብለው ዓባላት በከፍተኛ ተስፋ የጀመሩት ጉባኤ፣ ውስጥ ለውስጥ ሲንቀሳቀስ የነበረው ቡድን ከመጀመሪያው በራሱ ብድብቅ ተሰብስቦየራሱን አቋም ይዞ ነበር ወደ ጉባኤው የገባው። አቋሙ ባጭሩ እንዲህ ነበር፣ ከተሳካለት ድርጅቱን በራሱ ዓመራር ቁጥጥር ስር ለማስገባት ካልሆነ ደግሞ ድርጅቱ ለመበተን ነበር። ሆኖም ኢሕአፓ በብዙ ውጣ ውረድ ያለፉ፣ ተመሳሳይ ጥቃቶችን የተወጡና የተመከሮ ባለፀጋ ዓባላት ድርጅት በመሆኑ፣ ከፍተኛ ጥንቃቄና ትዕግስት በተሞላበት አካሄድ የድርጅቱን መሠረታዊ መርሆዎች በቆራጥነት ተከላክሎ የተቃጣውን አደጋ አከሸፈ። ድርጅቱንም ከብተና አዳነ። የውህዳኑ (አንጃ ሆኖ የወጣው) መሪ፣ ሁለቱም እቅዶቹ እንደከሸፉበት ሲያውቅ ጉባኤውን ረግጦ ሌሊቱኑ ሆቴሉን ለቆ ሄደ። በማግስቱ ጠዋት ጥቂት ተከታዮቹም እንዲሁ መድረኩን ረግጠው ተከትለውት ወጡ። ድርጅቱን ጎድተውከመሄዳቸው ባሻገር በጠላት ጎራ ሳይቀር ቀርበው ሊያእግዙት ሲነሱ ጊዜ አልፈጀባቸውም ።

ኢሕአፓን የከዳው አድርባይ መንገደኛ ከዛ አኩሪ ትውልድ አካል የወጣና ብሎም በኢሕአፓ ያለፈ ሲሆን፣ ነገር ግን ኢሕአፓን ተገን አድርጎ ሲቋምጥለት የነበረ ስልጣን በቀላሉ የማያገኘው መሆኑን ሲገነዘብ ድርጅቱን እንዳለ ላለው አገዛዝ እጅ መንሻ ለማድረግ ባደረበት ፍላጎት ዙሪያ በድርጅቱ ውስጥ የተለያየ ሺፋን በመጠቀም ዓላማውን በጣፋጭ ሃረጎች ቀብቶ በመንቀሳቀስ በፓርቲው ላይ ተደጋጋሚ ጥቃት ሲያደርስ ነው የቆየው ባንድ በኩል። በሌላ በኩል ደግሞ የድርጅቱ ዓባላት ከህዝብ ያልመነጨ ስልጣን ባፍንጫችን ይውጣ፣ የወሰደውን ጊዜ ቢወስድ ህዝብ የስልጣን ባለቤት እስኪሆንና አገራችንም ሏዓ ላዊነቷ እስኪከበር፣ ግንባራችንን ሳናጥፍ ትግሉን እንቀጥላለን ብለው የድርጅታቸውን አቋም ያለ ብዥታ ትግሉን ያስቀጠሉ የድርጅቱ ዓባላት ይገኛሉ።

በዚህ የአብዛኛው የድርጅቱ ዓባላት ፅኑ አቋም መፈናፈኛ ያጡት ጨለምተኞችና ስልጣን ጥመኞች በአንድ ወቅት ፋሽስቶችና ከዚያም አገር ገንጣይ ባንዳዎች እያሉ ሲያወግዙት ከነበረው አገዛዝ ጋር በጎን ተመሳጥረው ኢሕአፓን ተለጣፊ ድርጅት ለማድረግ አለያም ለማፈራረስና እንዳልነበረ ለማድረግ በድርጅት ውስጥ ቡድን በመፍጠር ተንቀሳቅሰዋል። ኢሕአፓ እልፍ አእዕላፍ ዓባላቱና ደጋፊዎቹ የወደቁለትን ዓላማና የሀገራችንን ሉአላዊነት በሚፃረር ከማንም ጋር አልራደርም በማለቱ እነዚህ ግለሰቦችና ቡድኖች የድርጅቱን መሪዎች በሬ ወለደ በሚል ክስ ስም ለማጉደፍ በውስጥና በውጭ ዘመቻ በመከፈት፣ አንድም አመራሩን ከዓባላት ለመነጠልና ለዚሁ ስንኩል ዓላማቸው ጋሬጣ የሆኑባቸውን የፓርቲው አመራር ዓባላትን ተደማጭነት ለማሳጣት፣ ሌላው ደግሞ ለስልጣን ያጨናል

ብለው ተስፋ የጣሉበትን አገዛዝ ለማስደሰት ታግለው የወደቁትን ጓዶች ከመቃብራቸው የሚያያንቀሳቅስ አሳፋሪ ድርጊቶችን ሁሉ ለመ ፈጸም ሞክረዋል። ቀደም ያሉት አንጃዎች በቀጥታ ከአገዛዙ /ከደርግ ጋር በመተባበር በፓርቲው ላይ እልቂትና ከፍተኛ ሰቆቃን ያደረሱ ሲሆን፣ የቅርብ ጊዜዎቹ ደግሞ (የአሁኖቹ) ምንም እንኳን እንደበፊቶቹ ከአገዛዙ ለመለጠፍ ሙከራዎች ቢያደርጉም፣ ጎጠኛው ወያኔ ድርጅቱን ሙሉ በሙሉ አለመቆጣጠራቸውን ሲያውቅ ብዙ ቢዳከሩም ጆሮ አልሰጣቸውም። በሌላ በኩል ሁኔታዎችም እንደመጀመሪያዎቹ በአካል ላይ ጉዳት እንዲያደርሱ አልፈቀዱላቸውም እንጅ ቢሆን ኖሮ ታሪኩ ሌላ ይሆን ነበር። ሆኖም እኒህኛዎቹ ለየት ያለ የማጥቂያ ዘዴ ቀይሰዋል። ይኸውም ከላይ ለመጠቆም የሞከርኳቸው ሁኔታዎች ከውስጥ ሲከሽፉባቸው፣ የድርጅቱን ህጋዊ መድረክ ረግጠው ከወጡ በኋላ እኛም ደምተንለታል እና ኢሕአፓ የሚለውን ስም ለማንም እንለቅም በማለት የፖለቲካ ወሮበላነትን ወደ አዲስ ሳይንስ ከፍ በማድረግ የድርጅቱን ልሳን፣ ስምና አርማ በመጠቀም ህዝብን ባስገረመ ዝቅጠት እኛ ዴሞክራሲያዊ ኢሕአፓዎች ስንሆን ሌላኛው አምባገነን ቡድን ነው በሚል ማምታታቱን ይኸው እስከዛሬ ተያይዘውታል። ሆኖም መሠረታዊ መነሻቸው ኢሕአፓን ለማፍረስ በመሆኑና አንድ አርጎ ሊያስኬዳቸው የሚችል አስፈላጊው ዓላማና ስነ ምግባር ባለመኖሩ እንደ ቡድን ለ ዓመ ት እ ን ኳን ተቻችለው መጓዝ አለመቻላቸውን ማንሳቱም አስፈላጊ መሰለኝ።

እነዚህን ክፍሎች የመራው የቀድሞ አመራር ዓባል፣ ነጭ ፀጉር የእንጨት ሺበት እንደሆነ ሁሉ "ኢሕአፓ ዴሞክራሲያዊ" በሚል የውሸት መታወቂያ ዛሬም ህብረተሰቡን ግራ በማጋባት በተዘዋዋሪ ለየሃገሪቱ ጠላቶች ክፍተት እያበጀላቸው ይገኛል፡፡ ጊዜ በቃህ ቢለውም፤ታሪክን (ከነበረው ያውም) ያበላሸ ሆኖ በቀቢጸ ተስፋ ቢናወጥም አላርፍ ብሎ ራሱን ነጋ ጠባ ለቅሌት መዳረጉ የሚታይ ነው ። ሲምፖሲየም ብሎ የሙት ሙቱን የሙታን መፈራገጥ ውስጥ የገባውም ለዚሁ ነው ። ለነገሩ ማ ከ24 ዓመት አገሪቱን በማጥፋት የተንቀሳቀሰውን ወያኔን ያካተተ ብሄራዊ ሸንጎ እንዲካሄድ በቅርቡ ጥሪ ማድረጉ የግለሰቡን አቋም ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ ሳይሆን፣ ትክክለኛ አቋሙ ምን እንደሆነ ቁልጭ አርጎ የሚያሳይ ነው። ቀደም ሲል በብዙ ዓመታት ውጣ ውረድ አብረውት ያለፉትን አመራር ጓዶቹን በአደባባይ ወጥቶ ከደርግ ርዝራዦችና ሌሎችም ፀረ-ኢሕአፓ ግለሰቦች የሚያራምዷቸውን መድረኮች በመጠቀም ሲያብጠለጥላቸው ከርሟል። ሆኖም ብዙ ሳይቆይ ተንኮሉና ሻጥሩ ሲከሰትላቸው በወራት ውስጥ ጥለውት ከሄዱ ጥቂት የሴራ ተካፋዮቹ ጋር በመሆን የፈጠረውን ስም ብቻውን ተሸክሞት እንደቀረ በመረዳት ይመስላል፣ ወትሮ እጅግ ይጠላቸውና አብሯቸው መታየት እንኳ ይከብደው የነበሩ ግለሰቦችን ኢሕአፓን ስለሚጠላ ብቻ፣ ሰሞኑን መድረክ ፈጥሮ በክብር እንግድነት ጋብዟቸዋል።

መቸም አንድ ሰው አንዴ ከድርጅት ስነምግባርና ከህብረተሰብ ማህበራዊ ቁጥጥሮች ውጭ ከወጣ ዝቅጠቱ በሚያሳዝን ሁኔታ እየባሰበት እንደሚሚሄድ ፍንትው አድርጎ የሚያሳየው ደግሞ የሰሞኑ "በኢሕአፓ ሲምፖዚየም ተገኙልን" በሚል የተሰራጨው በራሪ ወረቀት ላይ በእንግዳ ተናጋሪነት የተጋበዙትን ግለሰቦች መመልከት ይበቃል። ከነዚህ ተጋባዦች መካከል፣ አንድ ድርጅቱን ክዶ ወጥቶ ከዘረኛውና ስንት የድርጅቱን ዓመራሮችና የቆዩ ዓባላትን የጨፈጨፈው ወያኔ ጋር በግልፅ ሽር ጉድ ሲል የነበረው የቀድሞ ዓመራር ነበርኩ ባይ፣ ሌላው ደግሞ በምን ስሌት እንዳካተተው ባይገባኝም (ለነገሩ ግለሰቡ መርህ አልባ ከሆነ ሰንበት ብሏል)፣ የደርግ ደጋፊ የነበረና የሬዲዮ ጣቢያውን በኢሕአፓ ላይ ብዥታ ለመፍጠር የተነሱ ግለሰቦችን በማስተናገድ በዘመናት የተፈተነውን ድርጅት አፈርሳለሁ በሚል ከንቱ ተስፋ ሲያምታታ የነበረው ጋዜጠኛ ነኝ ባይ ሲሆን፣ ሶስተኛው ግለሰብ በአንድ ወቅት የኢሕአፓ አመራር ኮሚቴና የፖሊት ቢሮው ዓባል የነበረው፣ በ1960 ዎቹ መጨረሻና 1970ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በከተማው ለተወሰነ ጥበቃ ሲባል የተቋቋመውን የፓርቲው የትጥቅ አስኳል ለጥጦ ብዙ የድርጅቱ መሪዎች በደርግ የቀይ ሽብር ዘመቻ ሲሙቱና ሌሎቹም በታሰሩበት ወቅት በተፈጠረው ክፍተት ምክንያት፣ የማይጠየቅ ብቸኛ የፖሊት ቢሮ ስልጣኑን በመጠቀም፣ ብሎም በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ አስቦም ይሁን ሌላ ምክንያት ኖሮት፣ ለተወሰነ የውስጥ ደህንነት ጉዳዮች ጥበቃ ብቻ እንዲውል የተፈጠረውን የከተማ ስኳድ፣ እንዲያም ሆኖ እንኳን የ4 እና 5 የፓርቲው አመራሮችን ይሁንታ ካላገኘ ምንም ማድረግ የማይችል የነበረውን የፓርቲ ህዋስ፣ የግል ዓላማው ማራመጃ አድርጎ ለመጠቀም አጋጣሚው ፈ ቅዶለት ብዙ ጉዳት ያደረሰ ድርጅቱን ከተወ ቢያንስ ከሰላሳ ዓመታት በላይ የሆነው ግለሰብ ነው ።

ወታደራዊ ጁንታው በኢሕአፓ ዓባላትና ደጋፊዎች ላይ በአዋጅ ጦርነት ከፍቶ ከፍተኛ እልቂት እያደረሰና የፓርቲው ህልውና ራሱ አጠያያቂ ደረጃ በደረሰበት አደገኛ ሁኔታ ውስጥ እያለ፣ ታክቲካዊ ማፈግፈግን ሁኔታው ግድ በሚልበት ወቅት፣ የፓርቲው ከገጠር ወደ ከተማ በተራዘመ አመፅ የሚለውን መርሆ በመጣስ፣ ለያውም ያለ በቂ ትጥቅና ብዙውን ጊዜ በሚከሸፍ መሳሪያ፣ አደገኛ ሚሽኖች ላይ የሊግ ዓባላትን በማሰማራት ለቃጠሎው ነዳጅ፣ ለእልቂቱ አበረታች ሚና ተጫውቷል፡፡
ይኸው የፖሊት ቢሮ ዓባል፣ የከተማውን የመከላከያ ስኳድ መዋቅር ደህንነትን ባልጠበቀና በተዝረከረከ አያያዝ በቀበሌ ደረጃ ሳይቀር በማስፋት፣ እስከ ጥርሱ ከታጠቀው ሰው በላ ደርግ ጋር እንዲፋለም ቅፅ እና ቁጥር በሌለው፣ ራሱ ብቻውን በፃፈው ዴሞክራሲያ ልዩ እትም አማካኝነት " ህዝባዊ ትግሉ ይፋፋም፣ በፋሽስቶች መቃብር ላይ ህዝባዊ መንግስት ይቋቋም"" በሚል ጭራሽ ከተት ሠራዊት ብሎ ጦርነት አወጀ። ይህንን ሲያደርግ በሜዳ ያሉ አመራሮችን ለይስሙላ እንኳን ለማማከር ቢያንስ እንዳልሞከረ መጠቀስ ይኖርበታል። የቀድሞው ዓመራር ግለሰብ በሱ የተዛባ አመራር ለደረሰው እልቂት ሃላፊነትን የሚቀበል እንዳልሆነ በፈረንጆቹ 1980ዎቹ አጋማሽ ላይ ሱዳን እያለ በፓረቲው አመራር ዓባላት ተጠይቆ እንዲያውም እድሉን ዳግም ቢያገኝ ያንኑ ከማድረግ ወደኋላ እንደማይል ነበር ያስታወቀው። ሌላ ማለት ባይቻልም፣ ፍፁም ቀዝቃዛ ልቦና ያለውና ሃላፊነት የማይሰማው ግን የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ በሃላፊነት ቦታ ላይ የነበረ ግለሰብ ነበር ማለት ይቻላል። በታሪክ አጋጣሚ በመጀመሪያው ጉባኤ ላይ ተገኘ እንጂ መስራች እንዳልነበረ ደግሞ በጊዜው ተጋልጧል ።
ይህ በአንድ ወቅት የኢሕአፓ አመራርና የፖሊት ቢሮ ዓባል የነበረ ግለሰብ ከዛን ወቅት ድርጊቶቹ እና በኋላም ከድርጅቱ ከወጣ በኋላ ካደረጋቸው እንቅስቃሴዎች በመነሳት፣ ብሎም ያን የመሰለ ለብዙ የፓርቲው ዓባላትና ደጋፊዎች እልቂት ምክንያት የሆነ ሚናውን በተመለከተ ብዙ ማለት ቢቻልም፣ ለምን ይህን አደረገ ለሚለው ከሱ ከራሱ የተሰጠ መልስ ባለመኖሩ፣ ሁለት ግምቶችን ወይም ንድፈ ሃሳባዊ አስተያየቶችን መሰንዘር ይቻላል። አንደኛ፣ የፓርቲውን መከላከያ ስኳድ ተጠቅሞ፣ በከተማ የትጥቅ አመፅ በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ በነበረው ቀቢፀ ተስፋ የፓርቲው ህልውናም ሆነ የወጣቱ ህይወት ከማቀጣጠያ ጪራሮ አስበልጦ ማየት ያላስቻለው የስልጣን ጉጉት ነበረው፣ ወይም ደግሞ፣ በሁለተኛ ደረጃ፣ ግለሰቡ ፓርቲው ውስጥ ሆን ተብሎ የተተከለ ነበር፤ በመሆኑም ብሩህና አገር ወዳድ የሆነውን ትውልድ እስጨርሶ አገሪቱን ዛሬ እንደፈለጋቸው ለሚያደርጉ ነባር ጠላቶቿ ለማመቻቸት ተጠቅመውበት ሊሆን ይችላል ብለን የማንገምትበት ፍፁም ሁኔታ ሊኖር አይችልም።
ለሁለተኛው ግምት የበለጠ ክብደት የሚሰጡ ጉዳዮችን ማንሳት ይቻላል፣ ግለሰቡ በከተማ ያደረገውን አድርጎ ወደ ሜዳ ከሄደም በኋላ በአመራር ቦታው የፓርቲውን ሠራዊት ለመበተን የተጫወተው ሚና ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ሲሆን፣ በዚህ አጋጣሚ መነሳት ያለበት ሌላ ጉዳይ ግን፣ በጊዜው የነበረው የፓርቲው ዓመራር ኮሚቴ ይህን ግለሰብ አስከዛ ድረስ በአመራር ደረጃ እንዲቀጥል በመፍቀዱ ተወቃሽ እንደሚሆን በዚህ አጋጣሚ መነሳት ያለበት ጉዳይ ነው ።
ይህ ግለሰብ ከፓርቲው ዓመራርነትም ሆነ ከድርጅቱ ከወጣ በኋላ፣ አዳከሞት የሄደው ፓርቲ (ኢሕአፓ) መልሶ እንዳይቋቋምና ነባር ዓባላቶቹም ድርጅታቸውን ተመልሰው እንዳይቀላቀሉ በፈረንጆቹ በ 1992 ዓ . ም ፓርቲው ለቀድሞ ዓባላቱ ጥሪ ባደረገበት ወቅት፣ ከየት መጣ ሳይባል ( አድፍጦ እንደቆየ ህዋስ ) መድረክ በሚባለው ስብስብ አማካኝነት የፓርቲው ጥሪ እንዳይሳካ በቀጥታና በተዘዋዋሪ መንቀሳቀሱ፣ በየከተማዎቹ እየተዘዋ ወ ረ ለትግል የተነሳሱትን የቀድሞ ዓባላትም ሆኑ ከፓርቲያቸው ኢሕአፓ ጋር ሆነው በመታገል ላይ ያሉትን ዓባላት ከድርጅታቸው ለመነጠል መሯሯጡ፣ አገዛዙ ላይ የተነሳውን ቁጣ ለማለዘብ " ወያኔን በ ሰላማዊ የኢኮኖሚ የበላይነት ነው መታገል ያለብን፤ ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ አንድ አንድ ብር እንኳን ቢያዋጣ ... " የሚሉና ሌሎችም ተንበርክኮ ትግል መሰል አዘናጊ ታክቲኮች መጠቀሙን ማንሳት ግድ ይሆናል።
እዚህ ላይ መጠየቅ ያለበት፣ ይህ የቀድሞ አመራር በከተማ ትጥቅ ትግል የሚያምንና ይኸው እምነቱም የብዙ ሺ ዓባላትን ህይወት መስዋዕት ያረገውን ነባር አቋሙን መቀየሩንም ሆነ መከራከሪያ ምክንያቶቹን ይፋ ሳያደርግ በድንገት ተነስቶ " ወያኔን ለ መጣል በኢኮኖሚ የበላይነትን መያዝ ..." ይህን ለማስኬድ ደግሞ ባለ " አንዳንድ ብር መ ዋ ጮ "የሚል እንቶ ፈንቶ ው ከየት የመጣ ነው ? የሚለውና እንዲሁም "

ፖለቲካውን ወጣቱ እንዲመራው አዛውንቶቹ ቦታውን ይልቀቁ አይነት ተቀርቋሪ መሰል ግን መሠሪና ከፋ ፋይ ቅስቀሳ በተገኘባቸው አጋጣሚዎች ይሰብክ እንደነበር ሲታ ወ ቅ፣ (ሌሎች አቋማቸው እንዲሁ አወዛጋቢ የሆኑ ግለሰቦችም ይህንኑ አዘናጊ መስመር ሲገፉ መደመጣቸው በራሱ ግለሰቦቹ ከአንድ ምንጭ ወስደው የሚያስተጋቡት ሊሆን እንደሚችልም መገመት ይቻላል)። ስለዚህ የግለሰቡን ታሪክ ወደኋላ ሄደን ብንመረምር፣ ከላይ የተሰነዘረውን ግምት አጠናካሪ እንጅ አጠያያቂ አያደርገውም ለማለት ይቻላል። በመጨረሻ እርግጠኛ ዳኝነት ሰጭው የወደፊቱ የፓርቲውና የኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ሲፃፍ ብቻ መሆኑንም ማንሳቱ ተገቢ ነው። ይህ ግለሰብ ድርጅቱን ለማጥፋት ሲባዝን ዘመን ያለፈው ሆኖ ዛሬ በቀቢጸተስፋ በተዋጠው መሰሉ ስለ ድርጅቱ ተቆርቋሪ መስሎ እንዲቀርብ ዕድለ ማግኘቱ የሚያስገርም አይሆንም ።

ኢሕአፓ እጅግ ሰፊ ታሪክ ያለውና እውነተኛው ኢትዮጵያዊነት በዘመናዊ የፖለቲካ አደረጃጀት መልክ ራሱን የከሰተበት ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ቀደምት አባቶቻችን ና እናቶቻችን ለነፃነትና ለወገን ክብር ትተውልን ያለፉትን የአርበኝነትና የ አይበገሬነት ታሪካዊ ቅርስ ተረክቦ በጀግነነትና አያሌ መስዋዕት ከፍሎ የሀገርን ሉአላዊነትና የህዝቧን አንድነት ለማስከበር የታገለና እየታገለ የሚገኝ ድርጅት ነው።

ይህም በመሆኑ ኢትዮጵያን ለመበታተንና ዜጎቿንም ለማንበርከክ በስውርና በግልፅ ሲያሴሩ የቆዩ የሩቅና የቅርብ ጠላቶች ይህን ድርጅት እነሱ ከሚጠሉትና ከሚፈሩት አይበገሬ ኢትዮጵያዊነት ጋር አያይዘው ስለሚያዩት ለአንዴና ለመጨረሻ ለማጥፋት በግልፅና በስውር፣ በሁሉም አቅጣጫ ዘምተዋል። በድርጅቱ ውስጥ ሆነው ከከሸፉ እስከ አፈነገጡ የቀድሞ ዓባላትን በድርጅቱ ላይ ማሰማራት፣ ድርጅቱ እንዳያድግና በየትም ቦታ እንቅስቃሴው እንዲታገድ የጎረቤት ሀገሮችን ሳይቀር እንዳይተባበሩ በማስፈራራት፣ አዲሱ ትውልድ ስለ ኢሕአፓ አሉታዊ እይታ እንዲኖረው በሁሉም አቅጣጫ ታሪኩን ብረዛ በመደጎም፣ በውጭም ተምበርካኪ ምሁራንን ብቻ ሳይሆን ለዚሁ ተግባር ሲባል የተቋቋሙ የውሸት ተቃዋሚ ቡድኖችን አደራጅቶ በከፍተኛ ወጪ በማሰለፍ፣ በረቀቀ ሻጥር ድርጅቱ ድጋፍ አጥቶ እንዲዳከምና ሌሎች ብዙ ተመሳሳይ ሁኔታ ዎችን ማንሳት ይቻላል። ፀረ አትዮጵያ ሃይሎች ኢሕአፓን እንዲበተን ላለፉት 43 ዓመታት ያልፈነቀሉት ዲንጋይ አልነበረም ቢባል ማጋነን አይሆንም።

ይህን ማለት ደግሞ ከድርጅቱ የወጡም ሆኑ ያፈነገጡት ሁሉ በአንድ ወይም በሌላ ሃይል ተመርተው ነው ለማለት እንዳልሆነና ሁሉም ልዩነቶች መነሻቸውና መድረሻቸው አንድ ነው ለማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል። ግለሰቦች ከድርጅቱ ወጥተው ያለምንም አሉታዊ እንቅስቃሴ የግል ኑሯቸውን የሚገፉ እንዳሉ ሁሉ፣ ሌሎች ደግሞ ተስፋ በመቁረጥ ከትግል ሊገለሉና የራሳቸውን ድክመት የመቀበል ብቃት ሲያጡ መልሰው ትተውት የወጡትን ስብስብ ባገኙት አጋጣሚ የሚያብጠለጥሉም አሉ። ነገር ግን ሁሉም የጠላት ሴራ ተካፋዮች ናቸው ወደሚል ድምዳሜ መድረስ ደግሞ መሠረትን የሳተ ጅምላ ድምዳሜ ላይ እንደሚያደርስ ግልፅ ነው።

ምንም ተባለ ምን ይህ የኢትዮጵያን የፖለቲካና የማህበራዊ ግንኙነቶች ባህል ዝቅ የሚያደርግ፣ እኛ በሌለንበት እንዴት ኢሕአፓ ይኖራል? አይነት ድንቁርናና የወለደው 'ከኛ በላይ ላሳር' አስተሳሰብ በእድሜ ከገዘፉና ቀደም ሲል በድርጅቱ ካለፉ ግለሰቦች እንደ ገንቢ እንቅስቃሴ ሲገፋ ማየት፣ ያለብን ችግር ምን ያህል ስር እየሰደደ እንደመጣና ፣ የዘመናችን መርገም ሆኖ የተከሰተው ግለኝነትም እጅግ አሳሳቢ ደረጃ መድረሱን አመላካች ነው።

በመጨረሻም፡ ኢሕአፓ የሚለው ስም ነበርን የሚሉ ሁሉ ቀደው የሚካፈሉት አቡጀዴ አይደለም። ኢሕአፓ አንድና አንድ ብቻ ነው! ስለ ኢሕአፓም ተቅርቁሮ ሊናገር የሚችል የነበርን አፍራሽ መንጋ/አንጃ ሳይሆን ለድርጅቱ የሚቆረቆር፤ አባል ደጋፊ የሆነው ነው ። ድርጅቱን ሊያፈርሱ ሞክረው የከሸፈባቸው ልዩ ልዩ አንጃዎች ተሰብስበው ቢንጫጩ አንድም የዝንብ ክምችት መሶብ አይከፍትም ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ አሁንም ቢሆን የአፍራሽነትን ተልዕኮ አንጸባራቂ ነው ። ድርጅቱን ሊጎዱና ሊበታትኑ ሲጥሩ የቆዩ፤ ተደርግ እንጂ ከወያኔ እንጂ የድርጅቱ አካል ሳይሆኑ የቆዩ እንዴትስ በምን ተዓምርስ ስለድርጅቱ አንድነት ሊያወሱ ይችላሉ! እንዳለፉት የአንጃ ሴራዎች ሁሉ ይህም ውድቅ ሆኖ ያልፋል !!

ኢትዮጵያ በውድ ልጆቿ መስ ዋ ዕትነት ለዘላለም ተከብራ ትኑር!